# መለስ ዜናዊ የጀግናውን የአጼ ቴዎድሮስን መቃብር ለሱዳን ገበሬዎች ሸጠ (መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል)፣

ከገታቸው ጋረደው

ቅጥረኛው መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ በ1983 በሸቢያ ድጋፍ በኦነግ ትብብር፣ በአሜሪካ ትእዛዝ አትዮጵያን በወረሩ ማግስት ኤረትርያ የኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ስለሆ ነች ጻነቷን ማግኘት ይገባታል በማለት መለስ ዜናዊ ለተባሩት መንግስታት ዋና ጸሀፊ ማመልከቻ ስለጻፈ፣ በወቅቱ አዲስ የተሾሙት ዋና ጸሀፊ ቡጥሮርስ ቡጥሮስ ጋሊ ጉዳዩን ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ አንድ ተማሪ ሲገደል፣ ገዳዩ ተይዞ አልተቀጣም። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኤርትራን ህ ዝብ ፍላጎት አየተዘዋወረ ከመረመረ በኋላ በቁጥር የበለጠው ክፍል ከኢትያጵያ ጋር በፈደሬሽን ለመቀላቅል ሲወስን፣ በስምምነቱ መሰረት የኤርትራ ህዝብ የውስጥ አመራሩን ራሱ እንዲመራ፣ የፈደራሉ መንግስት የውጭ ጉዳይን መከላከያን ፣ ወደብን፣ ገንዘብን በሙሉ ስልጣን ሲመራ እንዱ፡በሌላው ጉዳይ ውስጥ እንዳይገባ፣ ስምምነቱን ለመጨመር፣ ለመቀነስ ውይም በሙሉ ለመስረዝ የሚችለው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ሰብሰባ በቻ ነው በማለት በቻርቸሩ አንቀጽ 91 አስፍሯል፣ ግን የድርጅቱ ዋና ጸሀፊ ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ፣ መለስ ዜናዊ፣ የኤርትራና የአሜሪካ መንግስታ ት ይህንን አንቀጽ ሆን ብለው ወደ ጎን በመተው ለድርጅቱ ጠቅላላ ስብሰባ ሳይሆን፣ ጉዳዩን በጓሮ በር ለጸጥታው ምክር ቤት በማቅረብ ኤርትራ የፖለቲካ ነጻነቷን አንድታገኝ ወሰኑ።

ከሃዲው መለስ ዜናዊ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አንጂ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም በማለት ኤርትራን ሲገነጥላት፣ አሱ ራሱን የቅኝ ግዛት መሪ በማድረግ አስመራ ሄዶ በግንጠላው ስነ ስርአት ሕያው ምስክር ለመሆን በቃ። እንደዚህ ያለን አሳፋሪ ከሀዲ መሪያችን ነው ብለን ስንቀበል አናፍርም? የአድዋ አርበኞች፣ የአምስቱ አመት ጀግኖች አንዴት ይታዘቡን?

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፌደራሉ ስምምነት የበላይ ጠባቂ ስለሆነ ስምምነቱን በሙሉ ለማፍረስ፣ ለመቀነስ፣ ለመጨመር የሚችለው የድርጅቱ ጠቅላላ ስብሰባ ብቻ ነው በማለት በቻርተሩ በአንቀጽ፡91፡ስለወሰነ፡ከላይ፡የተጠቀሱት አካላት ያሳለፉት ውሳኔ ህገ ወ ጥና በአለም አቀፍ ስምምነቱ ተቀባይነት የሌለው ነው፣የተባበሩት መንግስታትት ድርጅት የፌደራሉን ስምምነት ያጸደቀው በጠቅላላው ስብሰባ ኣንደመሆኑ ሁሉ ለማፍረስ ጠቅላላ ሰብሰባ ስለአልተሰበሰበ የመጀመሪያው ስምምነቱ ዛሬም አንዳለ የጸና ነው።

ይህንን ጽህፍ የጀመርነው መለስ ዜናዊ በቅርቡ በጎንደር ጠቅላይ ግዛት ያለውን የአርሻ መሬት ለሱዳን መንግስት ሸጠ ውይም ሸለመ ማለትን ስለሰማን፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ቢሆንም፣ መለስ ብለን ያለፈን ታሪክ ማውሳት የተገደድነው ፣ የኤሬትሪያን ግንጠላ ለመሰረዝ ሳይሆን፣ መለስ ዜናዊ አገር መሸጥ የጀመረው በጎንደር ሳይሆን በኤርትራ መሆኑን አዲሱ ተውልድ እንዲገነዘበው፣ የታሪኩን አመጣጥ ተከታትሎ ለወደፊቱ የአለኝታ ጥያቀውን ለማቅረብ ኣንዲያስችለው ለመርዳት ነው። የኤረትሪያ የፌደራል ስምምነት መፍረስና ነጻነት ማወጅ በተጭበረበር መንገድ መሆኑን ወጣቱ ትውልድ ጠንቅቆ መገንዘብ ይገባዋል።

መለስ ዜናዊ አትዮጵያን ወሮ ህዝቡን በጎሳ ከከፋፈለ በኋላ፣ በንጉሱ ዘመን የነበሩትን አስራ አራት ጠቅላይ ግዛቶች ወደ ዘጠኝ በመቀነስ ክወሎና ከጎንደር ጠቅላይ ግዛቶች ሰፊና ለምለም የእርሻ መሬቶችን ቆርጦ ወደ ትግራይ ክልል በመከለል፣ ነዋሪውን የወልቃይትና

የጠገዴ ህዝብ ተወልዶ ካደገበት አገር ንብረቱን ተነጥቆ በመላ አለም ተበታትኖ በስደት እንዲኖር አድርጎታል። ሁመራና አካባቢው በጣም ለም ስልሆነ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሰሊጥና ማሽላ ስለሚያፈራ የአገሪቱ ባለቤቶች በረሃብ ሲያልቁ  የትግራይ ህዝብ ካለትውልድ ስፍራው መጥቶት ጠቃሚ በመሆን ሀብታም ገበሬ ሆኖ በድሎት ይኖራል፣ ይህ አያሳዝንም? በቀልን አያስከትልም? የወልቃይት ህዝብ  ከአባቶቹ የወረሰውን መሬት ለትግራይ ገብሬዎች አስረክቦ እንዲሰደድ ያስገደደው በጊዘው የትግራይ ክልል ገዢ የነበረው  አቶ ገብሩ አስራት ነው። አቶ ገብሩ
 ከወልቃይት ህዝብ የነጠቀውን መሬት ለባለቤቱ በመመለስ ፈንታ፣ በ1983 በለንድን ስብሰ ባ ለኢሳይያስ አፈወርቂ የሸለመውን የአሰብን ወደብ አስመልሳለሁ እያለ ያሾፍብናል

መለስ ዘናዊ ባለፉት አስራ አምስት አመታት ያልሸጠው ያለወጠው ነገር  የለም። አሁን በሰሞኑ በጎንደር ግዛት  የአጼ ተዎድሮስን የትውልድ አገር ቋራን ለሱዳን መሸጡን፣
በአካባቢው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን የሱዳን መንግስት ማሰሩን ከዜና           ምንጮች ሰምተናል፡ ካልጠፋ መሬት መለስ ዜናዊ የአጼ ተዎድሮስን መቃብር ሸጠ? ደርቡሾች አጼ ዮሃንስን    ገለው    አንገታቸውን    በመቁረጥ    በግመል    ጀርባ    ላይ አስቀምጠው እንዳልተጫወቱባቸው፣ ዛሬ መልስ ዘናዊ የሱዳን  ወዳጅ በመሆን የጅግናው የቴዎድሮስን መቃብር የሱዳን ገበሬ የአርሻ ማሳ በማድረግ አጽማቸውን አውጥቶ ሊጥ
ለው አይደለም? መለስ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያለው ጥላቻና ንቀት ምን ያህል እንደሆነ ስላሳየን በመለስ ለይ የምንነሳው ዛሬ ነው። ሳይቀድመን ካልቀደምነው አይናችን እያየ አጽማችቸወን እውጥቶ እንድሚጥለው  የታወቀ ነው። መለስ በኢትዮጵያውያን ላይ ባለው ጥላቻ ንቀትና ትአቢት፣ እነዚህ ፈሪዎች ምን ያደርጉኛል፣ ያለኝን ህይል ላሳያቸው በማለት ባላፉት አመታትት እንዳዋረደን ሁሉ ለወደፊቱም መሳቂያ መሳለቂያ ያደርገናል ።

በአድዋ ጦርነትና በአምስቱ አመት ወረራ ጣልያን ኢትዮጵያን የወረረው የትግራይን መሬት መሸጋገሪያ በማድረግ ስለነበር. በዘመኑ የንበሩ የትግራይ ጀግና አባቶች፣ ክንዳችንን ሳንተራስ ጠላት የኢትዮጵያን መሬት አይረግጣትም በማለት ደማቹውን አፍሰው አጥንታትችውን ከስክሰው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ሳያስድፍሩ እንዳላስክበሩን ሁሉ. ዛሬ የእነዚህ ጀግና አባቶች ልጆች  መለስ ዜናዊ፣ በረከት ሲሞንና ስብሃት ነጋ የቴዎድሮስን መቃብር ማስደፈራችውን ቢመለከቱ እንዴት  ባዘኑ እንዴት ባላቀሱ ነበር፣ እነዚህ የታሪክ አተሎች፣ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ አንድነት ራሳችውን የሰዉ የጀግና መቃብር ሲሸጡ በቸልታ ብንመላከት የቋራው ጀግና ከመቃብሩ ቀና ብሎ እኛን የዛሬውን ትውልድ ቢመለክት እንዴት ባዘነብን፣ ለተዎድሮስ የምንከርፍለው ውልታ ይህ ነው? የአምስቱ አመት አርበኛ በላይ ዘለቀ በአምስቱ አመት ወረራ የጣሊያንን ባንዳ  መግቢያና መውጪያ አንዳላሳጣ ያህል፣ ..ሀይለ ስላሴ የሞት ፍርድ
ፈርዶበት፣ የመስቀያው ገመድ አንገቱ ላይ ካጠለቀ ብኋላ በመጨረሻ ትንፋሹ ኢትዮ
ጵያ  አገሬ ወንድ ልጅ አይብቀልበሽ  ብሎ የረገማት እርግማን ዛሬም ሲክተለን፣ እኛ ወንዶች ከእህቶቻችን የምንለየው ሱሪ በመልበሳችን ብቻ እንጂ ወንድነት የለንም፣ ይህንን አሌ ብንል መልኩን በአካል የማናውቀው  ቅጥረኛው ፈሪው መለስ ዜናዊ በቴሌቪሌ መስኮት በቀላጤ ለአስራ ሰባት አመታትት ባልገዛን ነበር።

ባለፉት ስድስት ወራት ምንም እንቅስቃሴ አላደረግንም  ለምን? ትግላችንን ከግቡ አደረስን ውይስ መለስ ዜናዊን አንበረከክነው? መለስ እንደሆነ በቀላሉ የሚበገር አይደለም፣ በተለይ በአሁኑ ሰአት መሪ ወይም ሰብሳቢ ስለሌለን ብዙ ውርደት ያደርስብናል፡፤ መለስ በተፈጥሮው ፈሪ ሆኖ እኛን የበለጠ ፈሪዎች አድርጎናል፣ ሁላችንም ለውጥ ስንመኝ ራሳችን ግደታውን በመፈጸም ፈንታ ሌላው እንዲታገልልን ሌላው እንዲሞትልን ስለምንፈልግ፣ የመለስን የስልጣን እድሜ የምናረዝምለት እኛው
ራሳችን ነን። የመለስ የመከላከያ ሰራዊት የአንድ  ጎሳ ጥርቃሞች ስልሆኑ ከራሳችው ጎሳ ሌላ አይገባባቸውም፣ መለስ እንደእስት መልኩን ሲለዋውጥ ትናንትና ያገለላቸውን

ኤርትራውያንን ዛሬ አስጠግቶ ሲያሸሞነሙናቸው በቅርቡ የኢሳይያስ ተቃዋሚዎች አዲስ አበባ ከተማ ተሰበሰበው ልዩነታቸውን እስወግደው በህብረት እንዲታገሉ ሲያቀራርባ ቸው፣ የመለስ ፍላጎት ኢሳይያስ ከተባረረ በኋላ ከነሱ መካከል ለእሱ ታዛዥ የሚሆነውን ሾሞ እሱ የሁለቱም አገሮች መሪ መሆን ይፈልጋል። መለስ ይህንን ካደረገ ተጨማሪ አዲስ ሀይል ስልሚያገኝ ፣ ኢትዮጵያ የጋራችን ኤረትሪያ
የግላችን እየተባለ ዝርፊያው ሲቀጥል ፣ማቆሚያ የለውም፡፤

መለስ ወስናችንን ያለ ጠባቂ ስለአስቀረው፣ ኢሳይያስ አንድ ጥይት ሳይቶክስ ግዛታችንን ስለያዘ ፣ የወያኔ ጀሌዎች የሻቢያን ሀይል ለመቋቋም ስለአልቻሉ፣ ያለ አንዳች የህይወት ዋስትና ሜዳ ላይ የበታተናቸውን የኢትዮጵያን መከላካያ ሰራዊት ስብስቦ ስለአዘመተ ወራሪዎች ሲሸነፉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮቻችን በከንቱ መስዋእት ሆኑ። በዚህ ጦርነት ወታደሮቻችን የሞቱት ወሰናችውን ለማስከበር ነበር፣ አሁን ደግሞ ኤርትራውያን ኢሳያያስን ለማስወገድ በሚያደርጉት ጦርነት ሱማሊያ ውስጥ እንደተደረገው ኤርትራውያንን ለመርዳት መዝመታችን አይቀሬ ነው፤፡ መለስ የኢትዮጵያን ወታደሮች ወደ ሱማሊያ የላከው ባለፈው አመት ሲሆን፣ በዚህ አንድ አመት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮቻችን ሲገደሉ፣ ሰላሳና አርባ አስከሬኖች በአንድ ጉርጓድ ሲቀበሩ ብዙውች አስከሬናቸው በገመድ እያተጎተተ የውሾች ምግብ ሆነዋል፡፤ በሱማሊያ ህዝብ ላይ የደረሰው እልቂት ብዙ ስልሆነ አንድ ቀን የበቀሉ ከፋዮች ልጆቻችን ናቸው፡፤

እኛ ጎረበታችንን የሱማሊያን ህዝብ ለመግደል ድፍረቱና ብቃቱ ካለን ይህንን ወንጀልእንድንሰራ የሚያስገድዱንን ነፍስ ገዳዮች ለምን አንገላቸውም ወይም ገለን ለምን አንሞትም? የእኛ ኢትዮጵያውያን ችግር ብዙ ነው፣ መታወቂያችን ፈሪዎችና ደሆች መሆናችን፣ ላንስማማ መስማማታችን በመጀመሪያ ደረጃ ስንገኝ፣ መተማመን የሚለውም ቃል አናውቀውም፣ መወነጃጀል በጥቂት ጥቅም የጠላት መሳሪያ መሆን በተለይ መለስና ወያኔዎች ስልጣን ከያዙ ወዲህ በህዝብ ስም መነገድ፣ ተባብረን ለመስራት የማንችል ስንሆን ለህዝብ ጥቅም እንሰራለን በማለት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ብዙ እስነዋሪ ስራዎችን እንሰራለን.፣ ለምሳሌ በተቃዋሚ መስክ የተሰማራውን ዶክተር በያነ ጴጥሮስ የሚባለውን ሰው እንመልከት፣ እንደወያኔ ታጋዮች መሳሪያውን በትከሻው ስንቁን በአህያ ጭኖ አዲስ አበባ ባይገባም፣ ወያነዎች በተሰበሰቡበት በመጀመሪያው ቀን በመካከላቸው ተገኝቶ ተካፍሏል፣ ኤርትራ ትገነጠላለች ሲባል ያለ አእንዳች ተቃውሞ ተቀብሏል፣ ሀገ መንግስቱን በተለይም አገርን ለመገነጣጠል የወጣውን አንቀጽ 39ን በደስታ አምኖ አጽድቋል። በሽግግሩ መንግስት በምክትል ሚኒስቴርነት አገልግሏል። አርባ ሁለቱ የዩኒቨስቲ መምህራን ከስራ ሲባረሩ እሱ አልተነካም ፣ ከዚያም በኋላ አስከ ዛሬ ድረስ ከምክር በቱ ሳይለይ ሁለት ደመወዝ እያገኘ ሰርቷል፣ ይሰራልም። በዚህ ጊዜ ለወከለው ህዝብ ያመጣለት መልካም ነገር አልተሰማም፣ በምክር ቤት በመቀመጡ የመንግስቱን አባላት በድምጽ ብልጫ ባያሸንፍም በተቃዋሚ ስም በመቀመጡ ድምጽ ሲቆጠር አንድ ተቃዋሚ ተገኝቷል ሲባል የመንግስቱን ዲሞክራትሪካዊ አሰራር ሲመሰክር የመረጠውን ህዝብ ጎዳ እንጂ አልጠቀመም፣
የዶክተር በየነ ጴጥሮስ አሰራር በዚህ አይነት ቢታዋቀም ለሎችም በብዛት ስለሚገኙ፣ የአገርን ጥቅም ለመጠበቅ መለስንና ግብረ አበሮችን አስውግደን ትክከለኛውን መንግስት ለማቋቋም የቤት ውስጥ ጠላቶቸንን መምክርና መመለስ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው፣ ይህንን ካላደርግን መለስ እንዳቀደው በታትኖን ሰለሚሄድ መጨረሻችን አንደፍልስጤም ህዝብ አገር አልባ ስደተኞች ሆነን ወቅረታችን ነው፡
ፍራንክፉርት ግንቦት 15 2000 23 05 2008